የሰ/መ/ቁ. 48608

ህዳር 2 ቀን 2003 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ብርሀኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወጋገን ባንክ (አ.ማ) - ኤፍሬም ፈቃዱ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሀብቶም ረዘነ ከጠበቃ ፊሊጶስ አይናለም ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የትግራይ ክልል የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡ ክርክሩ በብድር የተወሰደ ገንዘብን የሚመለከት ነው፡፡ በሥር ፍርድ ቤት አመልካች ከሳሽ ተጠሪ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ በብድር የወሰዱትን ብር 200,000 እና ይህ የብድር ገንዘብ የሚወልደው ወለድ በድምሩ 306,185.16 (ሶስት መቶ ስድስት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ አምስት ብር ከአስራ ስድስት ሣንቲም) እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በተከሳሽነት ቀርበው አመልካች መኪና ሸጧል እንደዚሁም ወለዱ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 2024(ረ) ይታገዳል የሚሉ መከራከሪያዎችን ያቀረቡ ሲሆን በዋነኛነት እዳዬን ሰርዞልኛል ምክንያቱም በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በደረሰብኝ ጉዳት ለመክፈል እንደማልችል ተረጋግጧል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች ተጠሪ በማስረጃነት የጠቀሱት የውስጥ መፃፃፊያ ነው፡፡ እዳው አልተሠረዘም የሚል ክርክር አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመዘነ በኋላ አመልካች ተጠሪ የተበደሩትን ብድር የሰረዘላቸው በመሆኑ ዕዳውን ተጠሪ (ተከሳሽ) የመክፈል ሀላፊነት የለበትም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ነሐሴ 19 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የተጠሪ ዕዳ ለጊዜው በተንጠልጣይ ሂሳብ እንዲቆይ (written off) አደረግን እንጅ እዳው የተሰረዘ መሆኑን ለተጠሪ አልገለፅንለትም፡፡ አንድ ዕዳ በተንጠልጣይ ሂሳብ መያዝ (written off) እና አንድን የብድር ዕዳ ሙሉ በሙሉ መሠረዝ የተለያዩ ናቸው፡፡ ፍርድ ቤቱ ይህንን ለማስረዳት ያቀረብናቸውን ማስረጃዎች በተሟላ መልኩ አላየልንም፡፡ ባንኩ ለተጠሪ ያበደረውን ብድር ሙሉ በሙሉ ምህረት አላደረገም፡፡ ተጠሪ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት የተበደሩትን ብድር እንዳይከፍል የፈጠረባቸው

መሰናክል የለም ስለዚህ ተገቢውን ማጣራት ሣያደርግና ሙያዊ በሆኑ ነገሮች የባለሙያ አስተያየት ሣይሰማ የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት እኔ በምኖርበት አካባቢ ጦርነት የነበረ መሆኑና በጦርነቱም ውድመት የደረሰ መሆኑ ፍርድ ቤቱ ዕውቅና ሊሰጠው የሚገባው ፍሬ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካች ብድር ሲያበድር በመያዣነት ይዞት የነበረውን ተሽከርካሪ በራሱ ፈቃድ በግንቦት ወር 1997 ዓ.ም ነፃ በማድረግ ለቆታል፡፡ ይህም ዕዳውን በምህረት መልክ መሠረዙን የሚያሣይ ነው፡፡ በባንኮች ዝርዝር ፖሊሲና ፕሮሲጀር መሠረት ሁለት አይነት የብድር ዕዳ ሥረዛዎች መኖራቸውን ለመረዳት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው "written off" የሚባለው ሲሆን ሁለተኛው ለዘለቄታው ተበዳሪውን ላለመጠየቅ የሚደረግ የዕዳ ሥረዛ ነው፡፡ አመልካች ለተጠሪ ያደረገው ሁለተኛውን አይነት የዕዳ ስረሳ ነው በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ እኔ ያደረክሁት (written off) እንጅ ለዘለቄታው ተበዳሪው ብድሩን እንዳይከፍልና እንዳይጠየቅ ምህረት አላደረግሁም በማለት የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር በፅሑፍ የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን ችሎቱም የአመልካችንና የተጠሪን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ በቃል ክርክሩም አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩት አመልካች የተጠሪን ዕዳ በተንጠልጣይ ሒሳብ እንዲያዝ (written off) ነው ያደረገው ወይስ ተጠሪ በዕዳው እንዳይጠየቅ ለዘለቄታው እዳውን በመሰረዝ ምህረት አድርጎለታል በሚለው ነጥብ ላይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እኛም በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነውን ይህንን ጭብጥ በአግባቡ ለመፍታት አመልካችና ተጠሪ የሚያቀርቡትን ማብራሪያና ደጋፊ ጽሑፎችን መመልከቱ ብቻ በቂ እንዳልሆነ ተገንዝበናል፡፡

አመልካችና ተጠሪ የሚከራከሩበት ነጥብ የባንኮች የዕዳ አመዘጋገብ እና የዕዳ ሥረዛን "ፕሮሲጀርና" አሰራር የሚመለከትና የሙያ ማብራሪያ የሚያስፈልገው ነጥብ ነው፡፡ ፍርድ ቤቱ ተከራካሪዎች የሚከራከሩበት ጉዳይ የልዩ አዋቂ ምስክርነትና ማብራሪያ የሚያስፈልገው ሆኖ በሚያገኝበት ሠዓት የልዩ አዋቂ ምስክር በመሰየም ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ማድረግ እንደሚገባው የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 136 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ አመልካች ግንቦት 12 ቀን 1997 ዓ.ም በፃፈው ደብዳቤ ዕዳውን ከእኔ በማናቸውም ጊዜ ላለመጠየቅ ሙሉ በሙሉ በመሠረዝ ምህረት አድርጎልኛል በማለት ያቀረቡት ክርክር የባንክ ባለሙያዎችን በመመደብና አስፈላጊም ከሆነ ከብሔራዊ ባንክና ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስለ ባንኮች የዕዳ አመዘጋገብና የእዳ ሥረዛና የምህረት ፕሮሲጀር ተገቢው ሙያዊ ማብራሪያ እንዲሰጥ በማድረግ አመልካች የተጠሪን ብድር በተንጠልጣይ ሒሳብ ነው የመዘገበው (written off) ነው ያደረገው ወይስ አመልካች የተጠሪን ዕዳ በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ላይጠይቅ ሙሉ በሙሉ በመሠረዝ ምህረት አድርጓል የሚለውን ጭብጥ መወሰን ሲገባቸው በጉዳዩ የልዩ አዋቂ ምስክርነትና ማብራሪያ ሣይሰሙ አመልካች የተጠሪን ዕዳ ሰርዟል በማለት የበታች ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. የትግራይ ክልል የምስራቅ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2. የምስራቃዊ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች የተጠሪን የብድር ዕዳ በተንጠልጣይ ሒሳብ ነው የያዘው (written off) ነው ያደረገው ወይስ ዕዳውን በማናቸውም ጊዜ ላይጠይቅ ሙሉ በሙሉ በመሰረዝ ምህረት አድርጓል በሚለው ነጥብ ላይ የልዩ አዋቂ በመመደብና በማስመርመር የልዩ አዋቂ የሚያቀርበውን ሙያዊ አስተያየት ከሰማ በኋላ እንድወስን ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343(1) መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

*የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡*

*ራ/ታ*